# *በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን !*


1) በሰላም ንዒ ........ 2
2) ሰላም ሰላም ለኪ ........ 2
3) እመቤቴ ማርያም ........ 2
4) ድንግል ማርያም ........ 2
5) ደስ ይበልሽ ........ 3
6) አማን በአማን (አማኑኤል) ........ 3
7) ተነሱ እንዘምር ........ 3
8) ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ ........ 4
9) መድኃኔዓለም አዳነን ........ 4
10) እናመስግነው ........ 4
11) እልል በሉ ........ 5
12) ንሴብሆ ........ 5
13) ደስ ይበለን ........ 5
14) አድርገህልኛልና ........ 6
15) የኃያል ኃያል ........ 6
16) ጻድቃን ብሩካን ........ 6
17) ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት ........ 7
18) ከክርስቶስ ፍቅር ........ 7
19) እልፍ አእላፋት ........ 7
20) የምስራች ተወለደ ........ 7
21) ዮም ሰማያዊ ........ 7
22) መወለደት ........ 8
23) መድኃኒነ ተወልደ ነዋ ........ 8
24) በጐል ሰከበ ........ 8
25) በቤተልሔም ተወልደ ........ 8
26) በበረት የተኛው ........ 8
27) በኮከብ መጽኡ ........ 8
28) እሰይ እሰይ ........ 8
29) ሰብአ ሰገል መጡ ........ 8
30) የምሥራች ........ 9
31) ስብሐት ለእግዚአብሔር ........ 9
32) እንደ ዮሴሕፍ በሆን ........ 9
33) በወንጌሉ ያመናችሁ ........ 9
34) አማን በአማን ........ 9
35) ክርስቶስ ተወልደ ........ 9
36) ዐቢይ ነቢይ ........ 9
37) ሖረ ኢየሱስ /ቁ 1/ ........ 9
38) ሰማያዊ ........ 9
39) በቃና ዘገሊላ /ቁ 1/ ........ 9
40) መጽአ ቃል /ቁ 1/ ........ 9
41) ዮሐንስ አጥመቆ ........ 10
42) በእደ ዮሐንስ ........ 10
43) እንዘ ሕፃን ልኅቀ ........ 10
44) እንዘ ስውር/ቁ 1/ ........ 10
45) ዮሐንስኒ ሀሎ ........ 10
46) አእኩትዎ ወሰብሕዎ ........ 10
47) ወረደ ወልድ ........ 10
48) በፍስሓ ወበሰላም ........ 10
49) እስመ እምዘርዓ ........ 10
50) በብዙ አኃጉር እየዞርክ ........ 10
51) ነድ ለማየ ባሕር ........ 10
52) ኀዲኀ ተሰዓ /ቁ 1/ ........ 10
53) ኀዲኀ ተሰዓ /ቁ 2/ ........ 10
54) እምሄሶ ........ 10
55) ዮሐንስ ........ 11
56) ስብሐት ለአብ ........ 11
57) መጽአ ቃል /ቁ 2/ ........ 11
58) ልዑል እግዚአብሔር ........ 11
59) ኸኸ ኃዲኀ ተሰዓ /ቁ 3/ ........ 11
60) በቃና ዘገሊላ /ቁ 2/ ........ 11
61) ሖረ ኢየሱስ /ቁ 2/ ........ 11
62) ወአንተኒ ዮሐንስ ........ 11
63) ተአምረ ወመንከረ ........ 11
64) ኢየሱስ ሖረ ........ 11
65) እንዘ ስውር /ቁ 2/ ........ 11
66) ይትባረክ እግዚአብሔር ........ 11
67) ዮሐንስ ክቡር ........ 11
68) ወተመሰሎ ........ 11
69) በከመ ሰማዕነ ........ 12
70) ክርስቶስ ተወልደ ........ 12
71) እግዚኡ መርሐ ........ 12
72) ውስተ ማኅፀነ ድንግል ........ 12
73) የዓለምን በደል ........ 12
74) ግነዩ ለእግዚአብሔር ........ 12
75) በጎል በጎል ........ 13
76) በዛሬው ጥምቀት ........ 13
77) አዳምን ያልተወው ........ 13
78) ዮሐንስኒ ........ 14
79) ከድንግል ተወልዶ ........ 14
80) ጥምቀተ ባህር ........ 14
81) መላእክት ይብልዋ ........ 15
82) የአምላክ ቸርነቱ ........ 15
83) በምን በምን ........ 15
84) ማርያም እንወድሻለን ........ 15
85) እንደ ኤልሳቤጥ ........ 16
86) የሥላሴን መንበር ........ 16
87) ሰላም ለኪ ........ 16
88) ጎሳ ልብየ ........ 17
89) እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ........ 17
90) እሴብህ ፀጋኪ ........ 18
91) አምላከ እስራኤል ........ 18
92) ሰዓሊ ለነ ቅድስት ........ 19
93) ተክለ ሃይማኖት ........ 19
94) ቃና ዘገሊላ ........ 19
95) በሠርጋችን ዕለት ........ 20
96) ወደ ምሥራቅ እዩ ........ 20

## 1) *በሰላም ንዒ*

በሰላም ንዒ ንዒ ማርያም/2/

አ.ዝ፡- ትናዝዘኒ/2/ ኃዘነ ልብየ

አ.ዝ፡- ምስለ ሚካኤል/2/ ወገብርኤል

አ.ዝ፡- ምስለ ሱራፌል /2/ ወኪሩቤል/2/

አ.ዝ፡- ምስለ ዑራኤል/2/ ወሩፋኤል

አ.ዝ፡- ምስለ ኩሎሙ/2/ ቅዱሳን

አ.ዝ፡- ምስለ ወልድኪ/2/ አማኑኤል/2/

## 2) *ሰላም ሰላም ለኪ*

ሰላም/2/ ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ

አ.ዝ፡-የሕይወት መሠረት የፍጥረት አለኝታ

ድንግል አደራሽን ሁኝልን መከታ

አ.ዝ፡- በላዔ ሰብ ዳነ ብዙ ነፍስ አጥፍቶ

ያንቺን ስም ለጠራ ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ

አ.ዝ፡- ተማጽነንብሻል ባማላጅነትሽ

ድንግል አደራሽን አማልጅን ከልጅሽ

አ.ዝ፡- እኛም ብንከተል በጎ ምግባርን

በሰላም በጤና እንኖራለን

## 3) *እመቤቴ ማርያም*

እመቤቴ ማርያም እመቤቴ/2/

ባንቺ ሰላደረ የሠራዊት ጌታ

እመቤቴ ማርያም ይድረስሽ ሰላምታ/2/

አ.ዝ፡- ሕይወቱን የሰጠው ፍጹም ለሠላም

ሁሉን የሚችል ያለ በአርያም

የአምላክ ማደሪያ ድንግል ማርያም

ጌታ የመረጠሽ እስከ ዘለዓለም/2/

አ.ዝ፡- የምድር ባለ ጸጎች ይማልዱ ፊትሽ

የሰማይ መላዕክት ምስጋና ያቅርቡልሽ

አሕዛብ ይንበርከክ ለሃያሉ ልጅሽ

ክብር ይገባሻል በእናትነትሽ /2/

አ.ዝ፡- ላንቺ ሊያስተላልፍ ገብርኤል ሠላምታ

ከንጉሥ ተልኮ ከሠራዊት ጌታ

ሠላም ላንቺ ይሁን ብሎ ያበሰረሽ

እመቤቴ ማርያም ምስጋና ይድረስሽ /2/

## 4) *ድንግል ማርያም*

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ

መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ

ሰውና አምላክን ያገናኘሽ

አ.ዝ፡- አባታችን ያቆብ በፍኖተ ሎዛ/2/

አሸልቦት እንቅልፍ ተኝቶ በጤዛ

ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ መሰላል

ምሳሌሽን አየ ማርያም ድንግል

አ.ዝ፡- መላዕክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ /2/

እንዳየ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ

ተስፋ አድርጎ ሲኖር የሰላሙን ዘመን

ይኸው ተፈጸመ ባንቺ በናታችን

አዝ፡- ባንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም /2/

ባንቺ ተፈፀመ የያዕቆብ ሕልም

ሰውና መላዕክተ ተለያይተው ሲኖሩ

በልጅሽ መወለድ ባንድላይ ዘመሩ

## 5) ደስ ይበልሽ

ደስይበልሽ/2/ ማርያም ንፅህይት ድንግል/2/

ደስይበልሽ ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ/2/

አ.ዝ፦ ሰላም እልሻለሁ ማርያም ድንግል
እንደ ብስራታዊው እንደ ገብርኤል
ላንቺ የተሰጠሽ ሁለት ድንግልና
አንደኛው በሥጋ ሌላው በኅሊና

አ.ዝ፦ ከዓለም ሁሉ ሴቶች ንፅህይት በመሆንሽ
ሰማያዊው ምሥጢር የተገለጸብሽ
የልዑል ማደሪያ ለመሆን ያበቃሽ
የጌታችን እናት በጣም ደስ ይበልሽ

አ.ዝ፦ የተነበየላት ሕዝቅኤል ነቢዩ
የተዘጋችው በር ብሎ በራዕዩ
ሳይከፍት ገብቶ ወጣ የሠራዊት ጌታ
ደሞ ከዚያ በኋላ ኖራለች ተዘግታ

አ.ዝ፦ ማርያም ስትጎበኛት ወደ ቤቷ ገብታ
ኤልሳቤጥ ዘመረች በመንፈስ ተሞልታ
በመኅፀኗ ያለው ዘለለ በደስታ
እኛንም ትጎብኘን ከጧት እስከ ማታ

## 6) አማን በአማን (አማኑኤል)

አማን በአማን/2/ አማኑኤል ተመስገን

መድኃኔዓለም ተመስገን

ለዚህ ፍቀርህ ምን ልክፈልህ

አ.ዝ፦ ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልፀው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደሰው በደል ብትቆጥር ጌታ
የኔስ ኃጢአቴ የለውም ቦታ

አ.ዝ፦ በየደቂቃው ኃጢአተ ሥሰራ
ሥሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም

አ.ዝ፦ ምህረትን ልከህ አድነኸ ዛሬ
ታከቶኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በደስታ እየሳበችኝ
በፍቅር በደስታ መኖር አቃተኝ

አ.ዝ፦ የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍፁም አይጥምም
እንደ በደሌ ሰላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

## 7) ተነሱ እንዘምር

ተነሱ እንዘምር/2/

በአንድነት ሆነን በዕልልታ/2/

ኸኸ/3/ ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር/2/

ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር

አ.ዝ፦ አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

አ.ዝ፦ አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው/2/
አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት የአንተ ሥራ የአንተ ልዕልና
ቢነገር አያልቅም ሰምህ ነው ገናና

አ.ዝ፦ ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ

በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ
ከእንቅፋት ከድንጋይ ትሠውረናለህ

አ.ዝ፡- ስለ መልካም ሥራህ አለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታህ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከ ማታ
ሌላ ምንም የለን የምንከፍልህ ጌታ

አ.ዝ፡- መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን እናውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከ ዘለዓለም ለስምህ እነዘምር

## 8) *ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ*

ንሴብሖ/2/ ለአምላከ እዝራ
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

አ.ዝ፡- ለምስጋና ቀሰቀሰኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ሰለፍቅርህ ልጀምር ማሕሌት
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

አ.ዝ፡- ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሐን
አስገረመኝ ከዋክብቱ ሲያወሩ ሥራህን
ንሴብሆ ለአመላከ እዝራ

አ.ዝ፡- አዕዋፋት በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው ያንተን ክብር በምስጢር ሲያወሩ
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

አ.ዝ፡- ከበሮ ሆይ ጸናፅል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

አ.ዝ፡- ኑበእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ስለሁሉም ነገር
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

## 9) *መድኃኔዓለም አዳነን*

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ/2/
ኸኸ ደስ ይበለን/2/ እልል በሉ/2/
አዳነን በማይሻር ቃሉ /2/
እናታችን ቅድስት የአምላክ እናት/2/
ኸኸ እንስገድላት/2/ በዕውነት/3/
ለአምላክ እናት/2/
ጻድቃን ሰማዕታት ወሐዋርያት/2/
ኸኸ ያማልዱናል/2/ መላዕክት/2/
በዕውነት በላይኛው ቤት /2/
ተዋህዶ ንፅህይት እንከን የሌላት/2/
እንከተላት/2/ እስከ ሞት/2/ በዕውነት ያለ ፍርኃት/2/

## 10) *እናመስግነው*

እናመስግነው/2/
አምላካችን ወለታው ብዙ ነው /2/

አ.ዝ፡- ከኃጢያት ገደል ከሞት ቤት ጎትቶ
መንግስቱን ለሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘላለማዊ ቤት ታላቅ ሐብት ያደለን
መቼም የማይተወን ታላቅ አባት አለን

አ.ዝ፡- ፍጡራን ቢንቁኝ መጎስቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋ ቢስ ነው ብለው
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መቶ ተወኝ
ሁለት እጄን ይዞ ልጄ ተነስ አለኝ

አ.ዝ፡- ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ላደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን
ለታላቅ ውለታው ጌታ ለዋለለን
በእልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን

## 11) *እልል በሉ*

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩ ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
ኢ.ዝ በኃጢያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትእዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላላለን ጠላቶቹ ስንሆን
ውለታው ብዙ ነው ክብር ለዕርሱ ይሁን/2/
ኢ.ዝ ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድሐኔአለም/2/
ኢ.ዝ ሕይወቱን የሰዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩ አይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያትወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ/2/
አዝ ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ /2/

## 12) *ንሴብሆ*

ንሴብሆ/2/ ለእግዚአብሔር/2/
ስቡሐ አዘተሰብሐ/2/
እናመስግነው/2/ እግዚአብሔርን/2/
ምስጉን ነው የተመሰገነ/2/
ኢ.ዝ፡- ባሕሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ
በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ
ከባርነት ቀንበር ፍጹም ነጻ ወጣን
ህይወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን
ኢ.ዝ፡- አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር
ጉልበታችን ቢዝል ፈተና ቢበዛ
ኃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ
ኢ.ዝ፡- ከዓለት የፈለቀ ውኃ ጠጥተናል
በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆኗል
ህዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

## 13) *ደስ ይበለን*

ደስ ይበለን/2/
አምላክ አለ መሐላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ስምህ
ኢ.ዝ፡- ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይችን ዕድሜ የጨመረልን
ለንስኃ ጊዜ የሰጠን
ኢ.ዝ፡- ኃጢአትህን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የፅድቅ ሕይወት
ኢ.ዝ፡- እልል በሉ የኀበኛችሁ
በምሕረት ዓይኑ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ

አ.ዝ፡- ድንግል ማርያም ትፀልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንድ እንዲያደርገን

## *14) ኢድርገህልኛልና*

አድርገህልኛልና በቸርነትህ አመሰግንሃለሁ እልል
ለዓለም/2/ አማኑኤል እገዛልሃለሁ ለዘላለም

አ.ዝ፡- ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
ይችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈፅሞ አራክልኝ የልቤን ትካዘዜ

አ.ዝ፡- አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ሁሉ ባንተ ታምኛለሁ

አ.ዝ፡- ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ በላገኝ ስጦታ
በቀንም በለሊት ሁሌ የሚያበራ
ምንክር ለባህሪህ እፁብ ያንተ ሥራ

አ.ዝ፡- አምላክ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሐብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎል እንደገና

## *15) የኃያል ኃያል*

የኃያላን ኃያል/3/ ልዑል እግዚአብሔር/2/
ታምራተ ብዙ በሰማይ/2/ በምድር/4/
ለአብና ለወልድ/3/ ለመንፈስ ቅዱስ/2/
መስገድ ይገባናል በሥጋ/2/ በነፍስ/4/
ለእግዝትነ ማርያም/3/ ለአምላክ እናት/2/
መስገድ ይገባናል የፀጋ/2/ ስግደት/4/
ለጻድቁ አባት/3/ ለተክለሐይማኖት/2/
መስገድ ይገባናል የፀጋ/2/ ስግደት/4/
ለጻድቁ አባት/3/ ለአቡነአረጋዊ/2/
መስገድ ይገባናል የፀጋ/2/ ስግደት/4/
ለጻድቁ አባት/3/ ለተክለሐይማኖት/2/
መስገድ ይገባናል የፀጋ/2/ ስግደት/4/

## *16) ጻድቃን ብሩካን*

አዝ፡- ጻድቃን ብሩካን አለምን ንቃችሁ
የክርስቶስን ፈለግ የተከተላችሁ
በመንግስተ ሰማይ እጥፍ ነው ዋጋችሁ

*ሰዓሉ ለነ አስተምሕሩ ለነ*
*እስመ በጸሎተ ጻድቅ ትድኅን ሐገረ/2/*

አዝ፡- ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስ ዲያቆን
ወቅዱስ ጊዮርጊስ መክብበ አሜን
ምሰለ ኢየሉጣ ወቂርቆስ ህጻን

አዝ፡- እሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ
ማእጠንተ መንበሩ ለአምላክ አዶናይ
መንበረ ጸባኦት ዘላዕላይ

አዝ፡- ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘእም አቅሌስያ
ወተክለ ሐይማኖት ዘኢትዮጵያ
ወማርቆስ አብ ዘእስክንድርያ

አዝ፡- ትንቢተ ነቢያት የተፈጸመብሽ
የኢያቄም እርግብ ማሪያም አንቺ ነሽ
ለምኚልን ለኛ በሃና በእናትሽ

## 17) *ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት*

ቤተክርስቲያነ ባሕረ ጥበባት/4/

አትመረመርም/2/ እጅግ ጥልቅ ናት/2/

በሥጋዊ መንገድ ለማወቅ ሲቃጣ

የእምነት መነፅሩን ይዞ ስላልመጣ/2/

አንዳንዱ በክህደት/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/

እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት/2/

ወላዲተ አምላክ/2/ መጠረተ ሕይወት/2/

እንመሰክራለን አማኑኤል  አለ ነው/2/

ሰው ሁሉ በክህደት/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/

## 18) *ከክርስቶስ ፍቅር*

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው/2/

መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መሰደድ ነው/2/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/

እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/

ሳይነጋ ተነሰተን እንግባ በጠዋት/2/

በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት/2

የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው/2/

ግነቡ ነጹህ ውኃ መሠረቱ ደም ነው/2/

ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት

ይኸው እዚህ አለ ያማኑኤል ቤት/2/

## 19) *እልፍ አእላፋት*

እልፍ አእላፋት ወትዕልፊት

ቅዱሳን ንጹሐን መላዕክት

ቆሙ ላገልግሉት ጸንተው ባንድነት

ቅዱስ /3/ አምላክ በማለት

አ.ዝ፡- ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት ሐገር

የሐይማኖት የፍቅር የምልክት ክብር

እውነት የታየብሽ የመላዕክት ክብር

አ.ዝ፡- እንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ

በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ

ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ

አ.ዝ፡- የሳጥናኤል ምኞት እንዳበባ ረግፎ

ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ

ሳጥናኤል ወደቀ እንዳበባ ረግፎ

አ.ዝ፡- ቅዱሳን መላእክት በእምነት የፀናችሁ

በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ

ስግደት ዘበ ጺጋ እንስገድላችሁ

## *የልደት መዝሙር*

## 20) *የምስራች ተወለደ*

የምስራች ተወለደ (ተጠመቀ) እሰይ እሰይ/2/

አማኑኤል /2/ የብርሃናት ጌታ የምስራቅ ፀሐይ ተወልደ አምላክ አዶናይ/2/

## 21) *ዮም ሰማያዊ*

ዮም ሰማያዊ በጐል ሰከበ ለዘተወልደ

እም ቅድስት ድንግል /2/

ርዕዎ ኖሎት /2/ አእኰትዎ መላእክት/2/

## 22) መወለደት

መወለደት ወልደ ዘበኩራ /2/

መንጦላዕተ ደመና ሰወራ /2/

## 23) መድኃኒነ ተወልደ ነዋ

መድኃኒነ ተወልደ ነዋ /2/

ይእዜኒ በሰላም ንትልዋ /2/

## 24) በጐል ሰከበ

በጐል ሰከበ በአፅርቅት ተጠብለለ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም /2/ ዮም ተወልደ /2/

በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ/2/

የዓለም መድኃኒት/2/ዛሬ ተወለደ/2/

## 25) በቤተልሔም ተወልደ

በቤተልሔም ተወልደ /2/ አማኑኤል/2/

እም ዘርዓ ዳዊት /4/ ተወልደ አማኑኤል/2/

## 26) በበረት የተኛው

በበረት የተኛው ቅዱሱ ህፃን

ለዓለም ሁሉ ሆነለት መድኅን/2/

ምሥክር ሊሆኑ ለፍፁም መንግስቱ

ትንፋሽ ገበሩለት ከበው እንስሳቱ/2/

እሰይ የምሥራች ሃሌ ሃሌ ሉያ

ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም/2/

## 27) በኮከብ መጽኡ

በኮከብ መጽኡ/2/ ሰብአ ሰገል/2/

ለአማኑኤል/4/ ይስግዱ ሰብአ ሰገል/2/

## 28) እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ ተወለደ እሰይ እሰይ ተጠመቀ

ከሰማየ ሰማያት ወረደ

ከድንግል ማርያም ተወለደ/4/

አዝ፡- እሱ ባይወለድ ቸሩ አምላካችን

እርሱ ባይወለድ እሱ ባይጠመቅ

መች ትገኝ ነበር ገነት ርስታችን

አዝ፡- ብርሃን ወጣላቸው በእውነት ወገኖቹ

በጨለማው ጉዞ እንዳይሰላቹ

አዝ፡- እንደ ጠል ወረደ ከሰማይ ወደኛ

ወገኖቹን ሊያድን ከከፉ ቁራኛ

አዝ፡-እግዚአብሔር አብ ላከ እንድያ ልጁን

እርሱ ወዷልና እንዲሁ አለሙን

## 29) ሰብአ ሰገል መጡ

ሰብአ ሰገል መጡ ይዘው እጅ መንሻ/3/

እጣን ወርቅ ከርቤ ለጌታ እጅ መንሻ /3/

ይኸው ተወለደ የዓለም መድሃኒት /3/

ይኸው ተጠመቀ የዓለም መድኃነኒት/3/

ይኸው ተወለደ የዓለም መድሃኒት /3/

ለእኛ ህይወት ሊሆን ለሰይጣን መጥፋት 3/

ትንቢት ተናገሩ ነቢያት በሙሉ /3/

አምላክ ቀዳማዊ ይወለዳል ሲሉ

አምላክ ቀዳማዊ ይጠመቃል ሲሉ

በሶርያ ታየ ፈጣሪ እንደ እንግደዳ/3/

ስርዓተ ጥምቀቱን ለህዝቡ ሊያስረዳ/3/

## 30) *የምሥራች*

የምሥራች ደስ ይበላችሁ/2/

የዓለም መድኃኒት ተወለደላችሁ ምሥራች ደስይበላችሁ/2/

የምሥራች ደስይበለን/2/

ጌታችን ተወልዶ አይተነው መጣን/2/

ንጉስ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ/2/

ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ/2/

ሰባሰገል እንደታዘዙት/2/

በኮከብ ተመርተው ህፃኑን አገኙት/2/

ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው/2/

ወርቅና እጣኑን ከርቤውንም ሰጡት/2/

## 31) *ስብሐት ለእግዚአብሔር*

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት/2/

ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብ ሃሌ ሉያ/5/

## 32) *እንደ ዮሴሕፍ በሆን*

እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ በሆን/2/

ኢየሩሳሌም/3/ በሆን አምላክ ሲወለድ ባየን/2/

## *የጥምቀት መዝሙራት*

## 33) *በወንጌሉ ያመናችሁ*

በወንጌሉ ያመናችሁ/2/

እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ/4/

## 34) *አማን በአማን*

አማን በአማን/2/ መንክር

መንክር ስብሐት ልደቱ/ጥምቅቱ /4/

እውነት በእውነት /2/ ድንቅ ነው
ድንቅ ነው የጌታ ልደት /2/

## 35) *ክርስቶስ ተወልደ*

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ/2/

አስተርእዮቱ አማን አስተርእዮቱ/4/

## 36) *ዐቢይ ነቢይ*

ዐቢይ ነቢይ /4/

ዮሐንስ ዐቢይ ነቢይ/2/

## 37) *ሖረ ኢየሱስ /ቁ1/*

ሖረ ኢየሱስ /4/

ዕም ገሊላ/3/ ኃበ ዮሐንስ/2/

ሄደ ኢየሱስ /4/

ከገሊላ /3/ ወደ ዮሀንስ /2/

## 38) *ሰማያዊ*

ሰማያዊ /6/

ተጠምቀ በማይ/2/ ሰማያዊ ኢየሱስ ናዝራዊ /2/

## 39) *በቃና ዘገሊላ /ቁ1/*

በቃና ዘገሊላ /2/

ዘገሊላ ከብካብ ኮነ/2/

## 40) *መጽአ ቃል /ቁ1/*

መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል /2/

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር /4/

መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል /2/

የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው /4/

## 41) ዮሐንስ አጥመቆ

ዮሐንስ አጥመቆ ለኢየሱስ /2/

በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዳኖስ /2/

## 42) በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/

ሰማያዊ /2/ ሰማያዊ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/

## 43) እንዘ ሕፃን ልኅቀ

እንዘ ሕፃን ልኅቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/

በዮርዳኖስ /4/ ተጠምቀ በዮሀንስ /2/

## 44) እንዘ ስውር/ቁ1/

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ /2/

ተአምረ ወመንክር ገብረ መድኃኒነ በቃና ዘገሊላ ከብካብ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ/2/

## 45) ዮሐንስኒ ሀሎ

ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ /2/

በሄኖን በቅሩበ ሳሌም /2/

## 46) አእኰትዎ ወሰብሕዎ

አእኰትዎ ወሰብሕዎ /2/

አእኰትዎ ወሰብሕዎ /4/

## 47) ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /6/

እም ሰማያት ወስተ ምጥማቃት /4/

## 48) በፍስሓ ወበሰላም

በፍስሓ ወበሰላም /2/

ወረደ ወልድ /4/ወልድ ውስተ ምጥማቃት

## 49) እስመ እምዘርዓ

እስመ እምዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ/2/

በቤቴልሔም ዘይሁዳ /2/

## 50) በብዙ አኃጉር እየዞርክ

በብዙ አኃጉር እየዞርክ የጌታን ወንጌል ያስተማርክ

የወንጌልን ቃል ግብር የገለጽክ ብፁዕ ነህ/2/ ዮሐንስ ደንቅ ነህ /2/

## 51) ነድ ለማየ ባሕር

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ /2/

ማየ ባሕረ ኀበ የሐውር ፀባቦ/2/

## 52) ኀዲጎ ተሰዓ/ቁ1/

ኀዲጎ ተሰዓ /4/

ወተሰዓተ /2/ ተሳተ ነገደ

## 53) ኀዲጎ ተሰዓ/ቁ2/

ኀዲጎ ተሰዓ ወተሰዓተ ነገደ /2/

ማዕከለ ባሕር /4/ ቆመ ማዕከለ ባሕር/2/

## 54) እምሄሶ

እምሄሶ ለሄሮድስ ይብላ መሐላሁ /2/

እምያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ/2/

ዐቢይ ነቢይ /2/ ሰባኬ ጥምቀት/2/

## 55) *ዮሐንስ*

ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት /2/

በረከትህ ይደር በእኛ ሕይወት/2/

## 56) *ስብሐት ለአብ*

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ/2/

ሃይማኖተ ጽኑ እንደ ዮሐንስ ወረደ /3/
መንፈስ ቅዱስ /2/

## 57) *መጽአ ቃል /ቁ2/*

መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውዕቱ ወልድየ/2/

ዘአፈቅር ሎቱ ስምዕዎ/2/

## 58) *ልዑል እግዚአብሔር*

ልዑል እግዚአብሔር /2/ ምስጋና ይገባሃል/2/

ለጥምቀት በዓል/2/በሰላም በጤና አደረስከን2/

## 59) *ኸኸ ኃዲጎ ተሰዓ /ቁ3/*

ኸኸ ኃዲጎ ተሰዓ ኸኸ ወተስዓተ ነገደ/2/

ኸኸ ማዕከለ ባህር ቆመ ማዕከለ ባህር/2/

ኸኸ ዘጠና ዘጠኙን ኸኸ መላዕክቱን ትቶ/2/

ኸኸ በባሕር መካከል ቆመ በባሕር መካከል2

## 60) *በቃና ዘገሊላ /ቁ2/*

በቃና ዘገሊላ ማየ ወይነ ረሰየ/2/

መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ/2/

## 61) *ሖረ ኢየሱስ /ቁ2/*

ሖረ ኢየሱስ/4/

እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ/2/

ሄደ ኢየሱስ /4/

ከገሊላ ወደ ዮሐንስ /2/

## 62) *ወአንተኒ ዮሐንስ*

ወአንተኒ ዮሐንስ ነቢየ ልዑል ትሰመይ /2/ ነቢየ ልዑል/2/

እስመ ተኃውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመትጼውር ፍኖቱ/2/

## 63) *ተአምረ ወመንከረ*

ተአምረ ወመንከረ ገብረ መድኃኒነ/2/

በቃና ዘገሊላ /2/ ከብካብ ኮነ/2/

## 64) *ኢየሱስ ሖረ*

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ ዕሴይ/2/

ዮሐንስ አጥመቆ በማየ/2/

## 65) *እንዘ ስውር /ቁ2/*

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ/2/

ወለማየኒ ረስየ ወይነ/2/

## 66) *ይትባረክ እግዚአብሔር*

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ/2/ እስራኤል/2/

ዘገብረ አቢየ ወመንከረ ባህቲቱ እግዚአብሔር/2/

## 67) *ዮሐንስ ክቡር*

ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል/2/

ብእሴ ሰላም/4/ ዘንብረቱ/2/ ገዳም/2/

## 68) *ወተመሰሎ*

ወተመሰሎ ሰብአ ዓይን አባግዓ ላባ ወማየ/2/

ለኃበ አባግ ዘዮም/2/ ወጥምቀተ አባይ/4/

## 69) *በከመ ሰማዕነ*

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርዒነ/2/

ወይነ ቃና/3/ በቤትከ ኮነ/2/

## 70) *ክርስቶስ ተወልደ*

ክርስቶስ ተወልደ ክርስቶስ ተጠመቀ ክርስቶስ ተወልደ/2/

ወለደነ ዳግመ/2/ እመንፈስ ቅዱስ ወማይ/2/

## 71) *እግዚኡ መርሐ*

ግዚኡ መርሐ ዮርዳኖስ አብጽሐ/2/

ወበ ህየ ዮሐንስ ወበህየ ፈጹመ ተፈሥሐ/2/

ጌታውን መራና ዮርዳኖስ አደረሰው /2/

በዚህም ዮሐንስ በዚህም በጣም ደስአለው /2/

## 72) *ውስተ ማኅፀነ ድንግል*

ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኃደረ ማኅፀነ ድንግል/2/

ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ /2/ በማይ ተጠምቀ/2/

## 73) *የዓለምን በደል*

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ

ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ

ፅድቅን ለመፈፀም በደልን አጥፍቶ

*የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ*

*አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ /2/*

አዝ፡- ባህር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ

ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ

እንደተናገረ ዳዊት በትንቢቱ

አዝ፡- ልጁ በዮርዳኖስ ፅድቅን ሲመሰርት

መጣ በደመና ሰማያዊው አባት

እየመሰከረ የልጁን ጌትነት

አዝ፡- እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ

በእርግብ ምሳሌነት ክንፉን አሰይፎ

አዝ፡- ባህር ስትጨነቅ ተራራው ሲዘምር

ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር

ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይንን ምስጢር

አዝ፡- የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉስ

ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ

ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ በመንፈስ

## 74) *ግነዩ ለእግዚአብሔር*

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር/2/

እስመ ለዓለም ምህሩ/4/ እስመ ለአለም/2/

እናመስግንሽ የዓምላክ እናት በዝማሬ/2/

የዓለም ቤዛ ነውና የማህፀንሽ ፍሬ/4/

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ/2/

መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ

በድንግልና የወለድሽው ክርስቶስ/2/

የድኩማኖች ብርታች ነው የህሙማን ፈውስ/4/

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችንን ፋቀ/2/

በቸርነቱ ጠብቆን ከበደል አራቀን /4/

ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ/2/

በመንግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ

ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ/4/

እመቤታችን እናታችን ማርያም/2/

የተማፀነሽ ይኖራል ለዘለዓለም/4/

ድንግልናሽም ሳይለመጥ ወልድን የወለድሽ/4/

ጌታችን እናት ማርያም እንቺ ነሽ/4/

## 75) *በጎል በጎል*

በጎል በጎል ሰብአ ሰገል/4/

በጎል ሰብአ ሰገል ሰገዱ ሎቶ/2/

አማን አማን አማን በአማን/4/

በዓለም ተሰበከ የጌታችን ቃል

በዓለም ተሰበከ የወንጌሉ ቃል

ፀሐይ ፀሐይ ፀሐይ ሰረቀ/2/

ፀሐይ ሰረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ /2/

አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ /2/

የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶልሽ

የዓለም መድሐኒት ተጠመቀብሽ/2/

ድንግል ማርያም ንፅህት ቅድስት /2/

የጌታችን እናት ምስጋና ይገባሻል

ከሴቶች ሁሉ አንቺ ተመርጠሻል/2/

እልል እልል ደስ ይበለን/2/

ወልድ ተወልዶ ነፃ አወጣን

ዮሐንስ ሲያጠምቀው ድልን አገኘን

አዲሱ ሙሽራ ሲመጣ ያያችሁ/2/

የዮርዳኖስ ሰዎች ስለምን ሸሻችሁ/2/

አዳምን ሊጠራ የመጣው ሙሽራ /2/

በገሊላ መንደር ለሰርግ የተጠራ/2/

ሰርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ/2/

የወይን ጠጅ ሆነ ውኃው ተለወጠ/2/

እናንተ ተራሮች እግር ሳይኖራችሁ/2/

እንዴት እንደጊደር ሽቅብ ዘለላችሁ/2/

ለመልካሙ ስራ በእምነት እንበርታ/2/

ከሰይጣን መገዛት ነፃ አወጣን ጌታ/2/

ወለደን በጥምቀት በመንፈስ ዳግመኛ/2/

የንጉሶች ንጉስ የፃድቃን እረኛ/2/

## 76) *በዛሬው ጥምቀት*

አዝ፡- በዛሬው ጥምቀት ተነግሮ አዋጅ
ነፃነት አገኘን በእግዚአብሔር አብ ልጅ

*ሽሽ እሰይ እሰይ ተጠመቀ /2/*

*ከሰማየ ሰማያት ወረደ /2/*

*በቅዱስ ዮሐንስ ተጠመቀ*

አዝ፡- አብ መሰከረለት በደመና ሳለ
የምወደው ልጄ ይኼ ነው እያለ

አዝ፡- ጌታ በዮሐንስ ሊጠመቅ ሲል ገና
ወደ ኋላ ሸሸ ዮርዳኖስ ፈራና

አዝ፡- እንደ አንበሶች ደቦል ተራሮች ዘለሉ
እፁብ ድንቅ ነው ግሩም ነው እያሉ

## 77) *አዳምን ያልተወው*

አዝ፡- አዳምን ያልተወው እንደተሰደደ
እሰይ የምስራች ዛሬ ተወለደ/2/
እሰይ የምስራች ዛሬ ተጠመቀ/2/

*አምላካችን መድኃኒታችን*

*ተወለደ ለነፃነታችን/2/*

አዝ፡ አዳምን ያልተወው እንደተጨነቀ
እሰይ የምስራች ዛሬ ተጠመቀ/2/

አዝ፡- አዳምን ሊጠራ የመጣው ሙሽራ
በገሊላ መንደር ለሰርግ ተጠራ/2/

አዝ፡- ሠርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ
የወይን ጠጅ ሆነ ውሃው ተለውጦ/2/
አዝ፡- እጅግ ያስደንቃል የጌታችን ስራ
በገሊላ መንደር ይህን ተአምር ሰራ/2/
አዝ፡- ጌታችን አንድ ቀን ያደረገው ተአምር
ሲያስደንቅ ይኖራል ይህን ሁሉፍጡር/2/

## 78) *<u>ዮሐንስኒ</u>*

ዮሐንስኒ ያጠምቅ/2/
በሄኖን /4/ በማእዶተ ዮርዳኖስ
አዝ፡- ዮሐንስ ሲያስተምር በጫካ በሜዳ
ግመል ጠጉር ለብሶ ሆኖ ምድረ በዳ
አዝ፡- አምላኩን የሚወድ ብዙ ሰው እያለ
ጌታውን ለማጥመቅ ዮሐንስ ታደለ
አዝ፡- ኮረብታው ይደልደል ጠማማውም ይቅና
እያለ ሰበከ ስርዓቱ ነውና
አዝ፡- ከኃጢአት ተለዩ በውሃ ተጠመቁ
መንግስት ሰማያት እንዳለች እወቁ

## 79) *<u>ከድንግል ተወልዶ</u>*

አዝ፡- ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ
ተጠመቀ ኢየሱስ ባሕረ ዮርዳኖስ
*ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ*
*ተጠመቀ ኢየሱስ ባሕረ ዮርዳኖስ*
አዝ፡- መጥምቁ ዮሐንስ ምንኛ ታደለ
ከበኒያት ሁሉ ስልጣኑ ከፍ አለ
አዝ፡- ትንቢቱን ሊፈፅም አሰቦ ክርስቶስ
ተጠምቆ አዳነን በባሕረ ዮርዳኖስ

አዝ፡- ምስጢረ ስላሴ ታየ የዛን ለታ
ምን ይከፈለዋል ለአምላክ ውለታ
አዝ፡- እመቤቴ ማርያም ምንኛ ታደልሽ
ከአዳም ልጆች ሁሉ አንቺ ተመረጥሽ
አዝ፡- ቸሩ አባታችን መድኃኒአለም
ኑ እናመስግነው በአንድነት ሆነ

## 80) *<u>ጥምቀተ ባህር</u>*

ጥምቀተ ባህር ዮርዳኖስ ንያ /2/
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/
አዝ፡- ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች
አልችለውም ብላ ወደ ኋላ ሸሸች
ብርሃነ መለኮት በወንዞች ሲሞላ
ዮርዳኖስም ሸሸ ሄደ ወደ ኋላ
አዝ፡- አብ በመጣ ጊዜ ደመናውን ጭኖ
በመንፈስ ቅዱስ ታየ በርግብ አምሳል ሆኖ
ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና
ቃሉን ተናግሮ ሆኖ በደመና
አዝ፡- ጌታችን ሲጠመቅ በ30 ዓመት
ባህር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት
ሰማይ ተከፈተ ሆነሽን ፀአዳ
ሚስጥረ ስላሴ ታወቀ ተረዳ
አዝ፡- እልል በይ ዮርዳኖስ የጥምቀት መገኛ
የፅድቅ መሰላል የድህነት መገኛ
ቀላያት አብርህት ብዙዎች እያሉ
እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

## 81) *መላእክት ይብልዋ*

መላእክት ይብልዋ/2/ ለማርያም
ሰላም እለኪ /4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ
ካህናት ይብልዋ/2/ለማርያም
ሰላም ለኪ/4/ይብልዋ ሰላም ለኪ
ዲያቆናት ይብልዋ/2/ ለማርያም
ሰላም ለኪ/4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ
መዘምራን ይብልዋ /2/ ለማርያም
ሰላም ለኪ/4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ
ደናግል ይብልዋ /2/ ለማርያም
ሰላም ለኪ /4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ
መነኮሳት ይብልዋ/2/ ለማርያም
ሰላም ለኪ /4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ
ምእመናን ይብልዋ/2/ ለማርያም
ሰላም ለኪ /4/ ይብልዋ ሰላም ለኪ

## 82) *የአምላክ ቸርነቱ*

አዝ- የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሐን
*ማርያም /3/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ*
*ባንቺ ሰላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /2/*
አዝ- መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ
አዝ- በቤተ መቅደስ ተቀምጣ ድንግል
ሀርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል
አዝ- ገብርኤል/2/ዜናዊ አዲስ
የአምላካችን መወለድ ስጋ መልበስ
አዝ- ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
አምላክ በርሷ አድር በመንበረ ግርማ
አዝ- እውነተኛ መልአክ መሆኑንም ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

## 83) *በምን በምን*

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን
ምሳሌ የላትም የላትም ክብሯን የሚመስል
አዝ- የሙሴ ፅላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሐም ድንካን
የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት የሩሩህን እርግብ/2/
አዝ- የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የእዝራ መሰንቆ የጌድዮን ፀምር
ደንግል እመቤት ናት የፃድቃኖች በር
ሆና የተገኘት የአምላክ ማህደር/2/
አዝ- የቅዱሳን እናት የአለም ንግስት
ችላ ተሸከመች መለኮተ እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስታርቀን ከዚህ አለም ጣጣ/2/
አዝ- ከማር ይጣፍጣል የድንግል መአዛ
አምላክን ታቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ፅዮን ይድረስሽ ምስጋና/2/

## 84) *ማርያም እንወድሻለን*

ማርያም እንወድሻለን/2/ ስለወለድሽ
የሕይወት ምግብን ማርያም እንወድሻለን
አዝ- ድከመቴን አትይ በሃጥያት መውደቄን
ተስፋዬ አንቺ ነሽ እስከ እለተ ሞቴ

ላልከዳሽ ምያለሁ ከስርሽ ላልጠፋ

ገፀ በረከቴ የሕይወት ዋስትና

አዝ- የምእመናን ውበት ዘውድ አክሊላቸው

ድንግል አንቺ እኮ ነሽ የመንገድ ስንቃቸው

ምስክር ነን ላንቺ እንደ ነቢያቱ

ስጦታ መሆንሽን ለአዳም ልጆች ሁሉ

አዝ- ሞገስና ፀጋ በጌታ ፊት ያለሽ

ከሰይጣን መሸሻ ዋስ ጠበቃችን ነሽ

እንዴት ነበር ያኔ ጌታን ስትወልጂ

የእረኞቹ ደስታ የመላእክት ዝማሬ

## 85) *እንደ ኤልሳቤጥ*

እንደ ኤልሳቤጥ ላመስግንሽ

ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ

የጌታዬ እናት የእኛ እመቤት

አዛኝነትሽ ከልብ ፍጹም የምህረት

አ.ዝ እርህራሄሽ ያስደንቀኛል

ስለኃጢያቴ ምልጃሽ ይቀድማል

የሰላምታሽ ድምጽ ደስ ያሰኘኛል

ከትካዜዬም ያሳርፈኛል

አ.ዝ ድምፅሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል

ሐዘኔ ቀርቶ ፊቴ ይፈካል

በእናትነት አንቺን የሰጠን

ቸሩ አምላካችን ይክበር ይመስገን

አ.ዝ የሁሉ እመቤት የሁሉ አፅናኝ

የአበው መድኃኒት ከአምላክ አገናኝ

ዛሬም በልቤ ደስታ ጨምረሽ

እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ

አ.ዝ ከሴቶች መካከል መርጦ ቀድሶሻል

ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉሻል

በልዩ ውዳሴ ያመሰግኑሻል

ድንግል እናታችን በቀኙ ቆመሻል

አ.ዝ የሰላምታሽን ድምፅ ልቤ ሲሰማ

ነፍሴ ደስ አላት ቀለለ ሸክሟ

ድንግል ላከብርሽ ስንበረከክ

እጅሽ ይዘረጋ ለመባረክ

## 86) *የሥላሴን መንበር*

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት

ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት

አእላፍ መላዕክት ሲሰግዱ በፍርሐት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት/2/

አ.ዝ የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት

ካህናተ ሰማይ ሥሉስ ቅዱስ ሲሉት

ይህን ታላቅ ክብር ሊያዩ የታደሉ

በጽድቅ ሥራቸው በምድር ይታያሉ/2/

አ.ዝ የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሐገር

ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን መንበር

ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ/2/

## 87) *ሰላም ለኪ*

ሰላም ለኪ /2/ ለኖኅ ሐመሩ

» » የአሮን በትሩ

» » የቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ

» » የጌድዮን ጸምሩ

» » የሰሎሞን መንበር ክብሩ

» » የፍሬ ስብሐትመዝሙሩ/2/

እመ እግዚአብሔር

ጸባኦት ሰላም ለኪ/2/

አ.ዝ ሰላም ለኪ መና ያለብሽ ንጹህ መሶብ

» » ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ

» » የይስሐቅ መአዛ/2/

እንዘ ንሴብሖ ለበረከትኪ

ዘሰምስለ እምኃ እሰግድ ለኪ/2/

አ.ዝ ሰላም ለኪ ሕብስተ መና ዘእሥራኤል

» » የሰማዕታት ንጹህ አክሊል

» » እፀጳጦስ ዘሲና

» » የኤልያስ መና/2/

እንዘ ንሴብሖ ለበረከትኪ

ዘምስለ ኦምሃ እሰግድለኪ/2/

## 88) ኀሳ ልብየ

ኀሳ ልብየ ቃለ ሰናየ/2/

ወአነ አይድ ቅዳሴሃ ለማርያም/2/

አ.ዝ እኔስ የማርያምን ውዳሴዋን እናገራለሁ

እንደ አባቴ ዳዊት በበገና እዘምራለሁ

ቀን ከሌሊት ሳልል ለምስጋና እተጋለሁ

የኃጢአቴ ቁስል እንዲፈወስ እጮሃለሁ

ምርኩዜ ነሽና እመቤቴ በአንቺ እመካለሁ

አ.ዝ እመቤቴ በእውነት እንወድሻለን

የእውነተኛ መብል ክርስቶስን ወለድሽልን

ምክንያተ ድሂን ሆይ ድንግል ማርያም የአምላክ መገኛ

በአማላጅነትሽ በመታመን እንጮሃን እኛ

ምሕረትን አድይን ኪዳነምህረት የዓለም መዳኛ

አ.ዝ ስለ ቸርነትሽ እመቤቴ ለእኔ እናቴ ነሽ

ስለ ንግሥትነትሽ እመቤቴ ነሽ

ዝናባት ሳያጠጡት አየራት ሳያሳድጉት

ሰማያዊ እንጀራ የሰጠሽን ቤተልሔማዊት

ቅድስተ ቅዱሳን የኖህ መርከብ የአምላክ እናት

አ.ዝ ቃና ዘገሊላ በሰርጉ ቤት በዚያ ተገኝተሽ ሳለሽ

ውኃውን ወደ ወይን ባንቺ ምልጃ እንዳስለወጥሽ

ዛሬም የእኔ ሕይወት ወይኑ አልቆ ባዶ ሆኖአልና

አንቺ የአምላክ እናት ንጽሂት ቅድስት ርኅሪሂተ ህሊና

ሕይወቴን አድሰሽ ቀድሰሽ ሙይው በምስጋና

## 89) እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ

እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ቸርነት አድርገህ /2/

እድሜ ለንስሃ እንደ ሕዝቅያስ ሰጥተህ

አ.ዝ አላቀውም ብሎ ሲጠየቅ ያመጸው

ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው

የጅረት ወንዝ ነው የሰጠኸው እንባ

ጴጥሮስ ተጸፅቶ ንስሃ እንዲገባ

አ.ዝ ጽዋው እንዳይደርሰኝ የይሁዳ እድል

ልጅህ ሆኖ ውሎ ኋላ ከመኮብለል

ጴጥሮስ እድለኛው አልቅሶ ተማረ

በትዕቢቱ ይሁዳ እንደወጣ ቀረ

አ.ዝ ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ

ለንስሐ ጠራት ጌታ በገሊላ

ታድሳ ተነሳች በእንባዋ ብዛት

እግሩ ሥር ተደፍታ ማርያም መግደላዊት

አ.ዝ አመጸኛው ልቤ ዛሬስ መች ይተኛል
በኃጢአት በዝሙት በስርቆት ይዋኛል
ወደ ቀድሞ ግብሩ እዳይመለስ
ፍቅርህ በእኔ ሰርጾ ኃጢአቴን ደምስስ

አ.ዝ በደላችንን ሁሉ ሳታስብ ትተህ
በምጽአት ሰዓት ከጻድቃን ቆጥረህ
ነጭ ልብስ ለብሰን ሆነን ከአንተ ጋራ
በሩ ሳይዘጋ አስገባን አደራ

## 90) *እሴብህ ፀጋኪ*

እሴብሕ ጸጋኪ ኦ እግዝእትየ ማርያም
ዕጽ ልምልምት ወፍሬ ጥዕምት /3/
ሐረገወይን /3/ አንቲ ማርያም
አጸደ ወይን /3/ አንቲ ማርያም

አዝ- ትመስሊ ፊደለ ወትወልዲ ወንጌለ
ወታገምሪ መስቀለ

አዝ- ትመስሊ ሰማየ ወትወልዲ ፀሐየ
ወታገምሪ አዶናየ

አዝ- ትመስሊ መሶበ ወትወልዲ ኮከበ
ወታጸግቢ ርኁበ

አዝ- ትመስሊ መቅደሰ ወትልዲ ንጉሠ
ወታገምሪ መንፈስቅዱስ

አዝ- ትመስሊ ታቦተ ወትወልዲ ጽላተ
ወታገምሪ መለኮተ

አዝ- ትመስሊ ደመና ወትወልዲ ኅብስተ መና
መታገምሪ ጥዒና

አዝ- ትመስሊ ገራህተ ወታፈርሂ ስዊተ
ወታጸድቂ ነፍሳተ

አዝ- ትመስሊ ስኒነ ወትወልዲ መድኅነ
ወትፌውሲ ድውያነ

አዝ- ትመስሊ ምሥራቀ ወትወልዲ መብረቀ
ወታለብሲ ዕሩሀቀ

አዝ- ለአብ መርዐቱ ለወልድ ወላዲቱ
ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ቤቱ

## 91) *አምላክ እስራኤል*

አምላከ እስራኤል ታማኝ ጌታችን
ለእስራኤል ለሙሴ የሆንከው መድህን
ፈርኦን እደገና በትእቢት ቢገን
ለእስራኤል አርበኛ መረጥከው ሙሴን

*አማላጅ ነው ገብርኤል (2)*
*የአምላክ ባለሟል የነአናንያ የነዳንኤል*

ረአዝ- ናቡከደነፆር ጣኦት አሰርቶ
ሰለስቱ ደቂቅን እንዲሰግዱ ጠርቶ
አንሰግድም ስላሉት ለእሳት ቢሰጣቸው
ገብርኤል ደረሰ ቆመ መሀከላቸው

አዝ- ቂርቆስ ከናቱጋር በእሳት ተጥለው
የእሳቱ ወላፈን ሳያቃጥላቸው
ተራዳኢው ገብርኤል ፈጥኖ ደርሶላቸው
እሳቱን ወደ ውሀ ቀይሮ አዳናቸው

አዝ- ሀርና ወርቁን በአንድ እየፈተለች
12 ዓመት ቤተ መቅደስ ኖረች
እመቤትነቷን እርሱ ስላወቃት
ሰላም ላንቺ ብሎ ገብርኤል ሰገደላት

አዝ- የመሳፍንቶቹን ጠብቆ ቃላቸው
ዳንኤልን ለአንበሳ ዳሪዮስ ቢሰጠው

ሳይበላው አደረ ሳይነካው አንበሳው
መልአኩ ገብርኤል አፉን ቢለጉመው

## 92) ሰዓሊ ለነ ቅድስት

ሰዓሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን /2/
እንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን
ለምኝልን እመቤታችን/2/

አ.ዝ- ተስፋ አንቺ ነሽና ለፍጥረተ ዓለም
እየተመኩብሽ እስከ ዘለዓለም
ኃጢአታቸው ተደመስሶላቸው
በአንቺ ፀሎት ዳነች ህይወታቸው/2/

አ.ዝ- ስምሽም ስልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃልኪዳን ገባልሽ ልጆችሽን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ/2/

አ.ዝ- ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትደክም ሲከባት ኃጢአት
መንገድ ጠፍቶን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን/2/

አ.ዝ- የልባችን ሐዘን እጅግ ከብዶብናል
ከበለሱ በታች በፍርሃት ወድቀናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደ ዘመድሽ
ደስ አሰኝን ይሰማን ድምፅሽ/2/

## 93) ተክለ ሃይማኖት

ተክለ ሃይማኖት ተክለ አብ
ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅድስ
አባታችን አማልደን አስታርቀን
ከፈጣሪ ጋር አምላካችን

አዝ- በሦስት ቀን ሥላሴን ያመሰገንከ
ከጭንጫ ድንጋይ ውኃ ያፈለቅከ
አባታችን ተክለ ሃይማኖት አማልደን
በኃጢአት እንዳንሞት
*አሽ... አባታችን ተክለ ሃይማኖት አማልደን*
*በኃጢአት እንዳንሞት*

አዝ- እንደ መላእክት ክንፍ የተሰጠህ
ሰማዕት ነቢይ አንድም ካህን ነህ
መምህራችን ሃዲስ ሐዋርያ
አስተምረን የፍቅር ባለሞያ
*አሽ... መምህራችን ሃዲስ ሐዋርያ*
*አስተምረን የፍቅር ባለሞያ*

አዝ- እንደ ሱራፌል በሰማይ ሲያጥን
በምድብር ነቢይ ሆኖ ማገልገሉን
በተሰጠው ፀጋ ሲያስነሳ ሙታን
ክህነት ካንተ ዘንድ ናት
አባታችን ፍታን ከኃጢአት
*አሽ... ክህነት ካንተ ዘንድ ናት*
*አባታችን ፍታን ከኃጢአት*

## 94) ቃና ዘገሊላ

ቃና ዘገሊላ (2)
በዚያ በሠርግ ቤት ተገኝተሻል ድንግል
ከልጅሽ ጋራ ተገኝተሃል ጌታ ከእናትህ ጋራ

አዝ- እድምተኞች ሞልተው የተጋበዙት
ሲበሉ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
ድንግል እናታችን ቤዛዊተ ዓለም
አንች ደረስሽለት ሆንሽው አማላጅም፤

አዝ- አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉም ይቻልሃል ወይኑን ሙላላቸው
ማድጋው ባዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው እመቤታችን ነሽ፤

አዝ- የጌታን አምላክነት የተገለፀበት
ምንኛ ታደለ የነዶኪማስ ቤት
ዛሬም ይሄው በሰርገኞች ቤት
በረከት ፈሰሰ በአምላክ ቸርነት፤

አዝ- ውሃው ተለውጦ ወይን ጠጅ ሲሆን
በቃና ዘገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ይኖራል በመካከላችን
ሁሌ ይሰጠናል ይህን የመሰለ ወይን

## 95) በሠርጋችን ዕለት

በሠርጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በእምነት ሆነን
ከእናትህ ጋራ ከእመቤታችን
ከመላእክት ጋራ ና በሰርጋችን
ከሐዋርያት ጋራ ና በሰርጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሰርጋችን

አዝ- በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳን ጌታ ስንጠራህ
የጥሪ ወረቀት ልከናል እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ክብር

አዝ- ነይ ከልጅሽ ጋር እመቤታችን
እንድታሟይልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶውን እንዲሞላ
በረከት የእርሱ ነው ቤታችሁ ይሙላ

አዝ- በጎደለው ሁሉ እየጨመርሺልን
ቤታችንን ሁሉ ሙይው እናታችን
ለአገልጋዩቹ ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖቹን ይሙሏቸው

## 96) ወደ ምሥራቅ እዩ

ወደ ምሥራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መውጫ
ድንግልን ቅረቧት እንበል ሃሌ ሉያ
ለአምላክ እናት ላዛኝቷ እልል እንበል እንዘምርላት (2)

አዝ- ወገኖች ተነሱ እናታችን መጣች
ስሟን ስንጠራ መቼ ትቀራለች
የተከዘን ልታጽናና ነይ ስንላት ትመጣለችና (2)

አዝ- የፅጌው ማኅሌት መዝሙሩ ሲጀምሩ
ማርያም ትመጣለች በደመና ባየር
ንዒ ስንል በሰዓታት ተስፋ አድርገን
ትመጣለች በእውነት (2)

አዝ- ፍልሰታ ሲጀመር ቃል ኪዳን ገብታለች
የሌሊት ውዳሴ ድንግል ትሰማለች
ሕፃናቱን በበረከት ልትጐበኝ
ትመጣለች በእውነት (2)

አዝ- በፍጹም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
ባማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ
እናታችን አለኝታችን
እንድናለን ድንግል አንቺ ይዘን (2)